# በሴቶች ላይ ለሚፈፀም
# የኃይል ጥቃት
# የወንጀል ፍትሕ አስተዳደሩ ምላሽ

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች:-**

ፀደይ ግርማ

ወንጀሎች በጥቃት አድራሽ ፆታ ተከፋፍሎ ስላልተቀመጡ የወንጀሉን ሙሉ ገፅታ ለማሳየት አስቸጋሪ ሁኔታ አጋጥሟል። በሴቶች ላይ የሚደርሱ የሀይል ጥቃት ወንጀሎችን ከሌሎች ወንጀል በመለየት መረጃ የመያዝ ስርዓት በፖሊስ እና አቃቢ ህጎች ዘንድ ቢዘረጋ በጥናቱ የተስተዋለውን የመረጃ እጥረት ክፍተት ይሞላል።ይህ መረጃም በፖሊስም ፣ አቃቢ ህግም ሆነ በፍርድ ቤቶች በፆታ የተለየ መረጃ ቢጠናቀር በሴቶች ላይ የሚደርስ የሀይል ጥቃትን በተመለከተ ግልፅ ምስል ለማግኘት፣ ያሉ የአፈፃፀም ችግሮችን ለመለየት እና በዚህ መረጃ ላይ ተመስርቶ የመፍትሄ ሀሳብ ለማቅረብ ያስችላል።ይሀም መረጃ በእነዚህ ወንጀሎች ረገድ ያለውን የተሟላ ምስል በመስጠት ወንጀሉን ለመከላከል እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ ውጤታማ እንዲሆን ይረዳል።

በሴቶች ላይ የሚደርስ የሀይል ጥቃት በአብዛኛው የሚፈፀመው በህፃናት ላይ በመሆኑ የህፃናትን ተጋላጭነት ለመቀነስ የመከላከል ስራዎችን ማከናወን አስፈላጊ ነው። በአንዳንድ መዝገቦች ግን ረጅም ጊዜ እየወሰዱበት ያሉበት ሁኔታ መነሻዎችን በመለየት የእርም እርምጃ ሊወሰድ ይ ገባል

በሴቶች ላይ ሚፈፀሙ ሀይል ጥቃት ወንጀሎች በአብዛኛው በቤት ውስጥ እንደመፈፀማቸው፣ በበህክምና ማስረጃዎች እና የሰው ምስክር መረጃ በዋነኝነት በመመስረት አቃቢህግ ክስ የሚመሰርት ስለሆነ በእነዚህ መረጃዎች አሰባሰብ ላይ ያሉትን ችግሮች ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት መግባባት ላይ ደርሰው ይህንን ችግር የሚቀረፍበት ሁኔታ ቢመቻች በሴቶች ላይ በሚፈፀሙ የሀይል ጥቃት ወንጀሎች በወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ የተሻሻለ አፈፃፀም ይኖራቸዋል።

በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ግኝት በዋስትና ከተለቀቁት ተጠርጣሪዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ ፍርድ ቤት ቢቀርቡም በፖሊሶች እና በአቃቢህጎች ተጠርጣሪዎች በዋስ ወጥተው መጥፋት በከፍተኛ ደረጃ ችግር ሆኖ መገለፁ እርስ በራሱ የሚቃረን ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ያለውን ብዥታ ለማጥራት ተጨማሪ ጥናት አስፈላጊ ነው።

በሴቶች ላይ የሚደርስ የሀይል ጥቃት በተመለከተ የሚፈፀመው እርቅ ላይ ከፖሊስሙ ሆነ ከአቃቢ ህግ የተገኘው መረጃ የተለያየበመሆኑ ፣ እርቅ ሚፈፀምበት ሁኔታ ፣ ስነስርዓትም ሆነ በእርቁ ሂደት የሚሳተፉ አካላት ላይ ወጥ ያልሆነ አሰራር ተስተውሏል። በተጨማሪም ባለሙያዎች የህክምና ወጪ የሚያስፈልገው ጉዳት ያለበትን እያስታረቁ ያለበት ሁኔታ አሳሳቢ ነው። በመሆኑም እርቅ የሚፈፀምበት ወጥ ሆነ አሰራር መዘርጋት አስፈጊ ነው።